መልእክት አሥር

## ሩት ግቧን መምረጧ፣ መብቷን መጠቀሟ፣ እረፍቷን መፈለጓ እና ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ሽልማት መቀበሏ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ሩት 1—4

**I. መጽሐፈ መሣፍንት ጨለማ እና ብልሹ የሆነው የእስራኤል አሳዛኝ ታሪክ መጽሐፍ ነው፤ የመሣፍንት አባሪ የሆነው መጽሐፈ ሩት ብሩህ እና ባለመዓዛ የሆነ የላቀ የጥንዶች ታሪክ ዘገባ ነው፤ በዚህ ታሪክ ውስጥ ያለችው ዋነኛዋ ገጸ-ባህሪ ሩት ከእሾህ መካከል እንደሚያድግ የሱፍ አበባ እና በጨለማው ሌሊት ውስጥ እንዳለ ብሩህ ኮከብ ናት—ሩት 1—4።**

**II. የመጽሐፈ ሩት ምዕራፍ 1 አቤሜሌክ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ካለው እረፍት ፈቀቅ ስለማለቱ (ቁ. 1-2)፣ ኑኃሚን በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ወዳለው እረፍት ስለመመለሷ (ቁ. 3-7፣ 19-22) እና ሩት ግቧን ስለመምረጧ (ቁ. 8-18) ይናገራል፡-**

ሀ. የሩት መጽሐፍ የእረፍት መጽሐፍ ነው፤ የሰንበት እረፍት በመልካሚቱ ምድር በከነዓን የተመሰለው እረፍታችን የሆነው ክርስቶስ ነው—ዘዳ. 12፡9፤ ዕብ. 4፡8-9፡-

1. እግዚአብሔር የሚሻውን ስላገኘ በሰባተኛው ቀን አረፈ፤ የእግዚአብሔር የልብ መሻት በምድር ላይ በመልኩ እንዲገልጠው እና በስልጣኑ እንዲወክለው ሰውን ማግኘት ነው—ዘፍ. 1፡26-28፤ ሮሜ 8፡28-29፤ 2 ቆሮ. 3፡18፤ ሮሜ 5፡17፣ 21፤ ራእ. 5፡9-10፤ 22፡5።
2. በብሉይ ኪዳን መልካሚቱ ምድር እረፍት ነበረች ምክንያቱም መቅደሱ በዚያ መገንባት ችሎ ነበርና፤ መቅደሱ የእስራኤል ልጆች ወደ መልካሚቱ ምድር የመግባታቸው ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ መጠናቀቅ ነበር፤ በመቅደሱ እግዚአብሔር ለመንግሥቱ፣ ለአገዛዙ እና ለአስተዳደሩ መገለጡን እና መወከሉን ማግኘት ይችላል—1 ነገ. 8፡1-11።
3. ክርስቶስ ለቅዱሳን በሦስት ደረጃዎች እረፍት ነው፡-
   ሀ. እግዚአብሔርን የገለጠው፣ የወከለው እና ያረካው እንዲሁም ከሥራው የሚያርፈው እና በሰማያት በእግዚአብሔር ቀኝ የሚቀመጠው ሰማያዊው ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ዘመን በመንፈሳችን ያለ እረፍታችን ነው፤ እንደ እረፍታችን ፍጹም ሰላማችን እና ሙሉ እርካታችን ነው—ማቴ. 11፡28-29።
   ለ. ሰይጣን ከምድር ከተወገደ በኋላ (ራእ. 20፡1-3) በሺህ ዓመቱ መንግሥት፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ እና በድል-ነሺዎቹ አማኞች ይገለጣል፣ ይወከላል፣ ይረካል፤ ከዚያም ክርስቶስ ከመንግሥቱ ጋር ከእርሱ ጋር አብረው-ለሚነግሡት እና እረፍቱን ለሚካፈሉት እና ለሚደሰቱት ለድል-ነሺዎቹ ቅዱሳን (ቁ. 4፣ 6) ሙሉ የሆነ እረፍት ይሆንላቸዋል።
   ሐ. በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድር፣ የመጨረሻው ጠላት የሆነውን ሞትን ጨምሮ ጠላቶቹ ሁሉ ለእርሱ ከተገዙለት በኋላ (1 ቆሮ. 15፡24-27)፣ ክርስቶስ እንደ ሁሉን-አሸናፊው ማንነት በእግዚአብሔር ለተዋጁት ሁሉ ለዘላለም ሙሉ የሆነ እረፍት ይሆንላቸዋል።

ለ. አቤሜሌክ መልካሚቱን ምድር ትቶ መውጣቱ ማለት በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ካለው እረፍት ፈቀቅ እያለ፣ ከዚህም የተነሣ ራሱን ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ እየለየ ነበር ማለት ነው፤ የመልካሚቱ ምድር የላይኛው ክፍል በሆነው በይሁዳ ከምትገኘው (ዘፍ. 49፡8-10፤ ዘጸ. 3፡8፤ ዘዳ. 8፡7-10) የሚመጣው ክርስቶስ የትውልድ ቦታ ከሆነችው ከቤተልሔም (ሚክ. 5፡2፤ ሉቃ. 2፡4-7) የጣዖት አምልኮ አገር ወደሆነችው ወደ ሞዓብ (መሣ. 10፡6) ፈቀቅ አለ።

ሐ. የኑኃሚን ወደ ቅድስቲቱ ምድር መመለስ የክርስቶስ የትውልድ ስፍራ ወደ ሆነችው ቤተልሔም ለመድረስ (ሩት 1፡19፣ 22) የጣዖት አምልኮ አገር ከሆነችው ከሞዓብ ወደ የአማኑኤል ምድር ወደ ሆነው ይሁዳ (ኢሳ. 8፡8)፣ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ወዳለው እረፍት መመለሷ ነበር፤ ክርስቶስን የሚመለከተውን ኢኮኖሚውን ለመፈጸም በእግዚአብሔር ከተሰጠቻት ምራቷ ከሆነችው ሩት ጋር ተመለሰች (ቁ. 22)።

መ. ሩት ከእግዚአብሔር ምርጦች ጋር ክርስቶስን በመደሰት ውስጥ የመሳተፍን ግብ መረጠች፣ ክርስቶስን ወደ ሰው ወገን ውስጥ ለማምጣት የረዳች ታላቅ ዋጋ ያላት የክርስቶስ የዘር ሐረግ ሆነች፤ ይህ ክርስቶስን ለሚመለከተው ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መከናወን እግዚአብሔርን እና መንግሥቱን መምረጧ ነበር—ማቴ. 1፡5-6።

**III. መጽሐፈ ሩት ምዕራፍ 2 የእግዚአብሔርን ምርጦች ርስት የበለጠገ ምርት ለመካፈል ያላትን መብቷን በመጠቀም ከአረማዊ መነሻ ታሪኳ ወደ እግዚአብሔር ስለተመለሰችው ስለ ሩት ይናገራል፡-**

ሀ. የመጻተኛ፣ የድሃ እና የመበለት በሆነው ሦስት-እጥፍ ደረጃዋ መሠረት፣ ሩት መከሩን ለመቃረም መብቷን ተጠቀመች፤ መቃረሚ ልመናዋ ሳይሆን መብቷ ነበር።

ለ. የመከሩን መታጨድ በተመለከተ የእግዚአብሔር ድንጋጌ የእስራኤል ልጆች የእርሻቸውን ድንበር እና የመከሩን ቃርሚያ ለድሆች፣ ለመጻተኞች፣ ወላጅ ለሌላቸው እና ለመበለቶች ከተዉ ያሕዌ እንደሚባርካቸው ነበር—ዘሌ. 23፡22፤ 19፡9-10፤ ዘዳ. 24፡19።

ሐ. ቦዔዝ ይህን ድንጋጌ ታዘዘ፣ በዚህም በያሕዌ የነበረውን ታላቅ እምነት መሰከረ፤ በእግዚአብሔር ሉአላዊነት ይህ ድንጋጌ ለአንድ ሰው—ለሩት—የተጻፈ ይመስላል።

መ. ሩት ወደ መልካሚቱ ምድር ከመጣች በኋላ የምድሪቱን ፍሬ ለመደሰት መብት እንደነበራት እንዲሁ፣ እኛም ወደ ክርስቶስ ውስጥ ካመንን በኋላ እርሱን እንደ መልካሚቱ ምድራችን የመደሰት መብት አለን፤ ሩት የመልካሚቱን ምድር ምርት ወስዳ የራሷ ለማድረግ መብቷን መጠቀሟ የሚያመለክተው ወደ ክርስቶስ ውስጥ ካመንን እና በ"ሚተባበር" መንፈሳችን (ሮሜ 8፡16፤ 1 ቆሮ. 6፡17) ከእርሱ ጋር ሕይወታዊ በሆነ መንገድ ከተጋጠምን በኋላ፣ ክርስቶስን ለማትረፍ፣ የራስ ለማድረግ፣ ለመለማመድ እና ለመደሰት እርሱን መከታተል መጀመር አለብን (ፊልጵ. 3፡7-16)።

ሠ. መጽሐፈ ሩት ኃጢአተኞች በክርስቶስ ውስጥ የሚሳተፉበትን እና ክርስቶስን የሚደሰቱበትን መንገድ፣ ስፍራ፣ ብቃት እና መብት በስዕል ያሳያል፤ በእግዚአብሔር ድንጋጌ መሠረት፣ ወደ ክርስቶስ ውስጥ ያመንን እኛ ክርስቶስን የመደሰት መብታችንን ለመጠየቅ ብቁ ተደርገናል መቆሚያም አግኝተናል (ቆላ. 1፡12፤ ራእ. 2፡7፤ 22፡14)።

ረ. እንደ ትረካ፣ መጽሐፈ ሩት የሚወደድ፣ የሚነካ፣ የሚያሳምን እና የሚያሸንፍ ነው፤ በምዕራፍ 2 በሚገኘው መዓዛ ባለው ታሪክ ውስጥ አራት ምሳሌዎች ተመልክተዋል፡-

1. በሀብት ባለጠጋ የሆነው ቦዔዝ (ቁ. 1) በመለኮታዊው ጸጋ ባለጠጋ የሆነውን ክርስቶስ (2 ቆሮ. 12፡7-9) በምሳሌ ያሳያል።
2. በእግዚአብሔር ቃል የተገባው የመልካሚቱ ምድር እርሻ (ሩት 2፡2-3) ለእግዚአብሔር ምርጦች የሕይወት አቅርቦት የመንፈሳዊና የመለኮታዊ ፍሬዎች ሁሉ ምንጭ የሆነውን ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ (ፊልጵ. 1፡19-21) በምሳሌ ያሳያል።
3. ገብስ እና ስንዴ (ሩት 2፡23) ለእግዚአብሔርም ለሕዝቡም ምግብ ለመሥራት እንደሆነ ግብአት (ዘሌ. 2፤ ዮሐ. 6፡9፣ 33፣ 35) ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል።
4. ከእግዚአብሔር ተስፋ ቃሎች የራቀች አረማዊ ኃጢአተኛ የሆነችው ሞዓባዊቷ ሩት (ዘዳ. 23፡3፤ ተዛ. ኤፌ. 2፡12) ከእግዚአብሔር ምርጦች የመከር ቃርሚያ እንድትካፈል መብት መሰጠቱ ከእግዚአብሔር ምርጦች ልጆች ድርሻ ጠረጴዛ ሥር እንዳለ ፍርፋሪ ክርስቶስን እንዲካፈሉ እድል የተሰጣቸውን አሕዛብ "ውሾች" (ማቴ. 15፡21-28 እና በቁጥር 27 ላይ የግርጌ ማስታወሻ 1) በምሳሌ ታሳያለች።

## IV. የመጽሐፈ ሩት ምዕራፍ 3 ሩት እረፍቷን ስለመፈለጓ ይናገራል፡-

ሀ. የሩት አማት የሆነችው ኑኃሚን ልጄ ሆይ፣ የምታርፊበትን ስፍራ ልፈልግልሽ ይገባል አለቻት—ቁ. 1፡-

1. ኑኃሚን የሩት ባል ለመሆን ተገቢ የሆነው ሰው ቦዔዝ እንደሆነ ተገንዝባ ነበር፤ በመሆኑም ሩት እንድታገባ ለመገፋፋት እንደ "አገናኝ" አገለገለች።
2. እውነተኛ የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች ክርስቶስን እንደ ባላቸው ይወስዱት ዘንድ እንደ ሙሽራቸው እንዲወዱት በክርስቶስ ውስጥ የሆኑ አማኞችን በማነሳሳታቸው እንደ ኑኃሚን ናቸው—2 ቆሮ. 11፡2፤ ራእ. 19፡7፤ 21፡9-10።
3. እረፍት የምናገኝበት ብቸኛው መንገድ ክርስቶስን እንደ ባላችን መውሰድ ነው፤ ከእርሱ ጋር የቅርብ እና በጣም የቅርብ በሆነ ግንኙነት በመኖር እርሱን እንደ ባላችን ማወቅ እና እንደ ባላችን መውሰድ አለብን—1 ቆሮ. 2፡9፤ ተዛ. 16፡22።
4. ክርስቶስን እንደ ባላችን በመውሰድ ካገባነው ሕይወታችን ይለወጣል፤ የሚስት ታማኝነት ሊኖረን እንደሚገባ እንገነዘባለን፣ ከእርሱ ጋር አንድ ሆኖ በተገቢ ሁኔታ በመመላለስ ክርስቶስን እንደ ሕይወታችን እና ማንነታችን እንዴት መደሰት እንዳለብን እንማራለን—2 ቆሮ. 2፡10።

ለ. ሩት ወደ መልካሚቱ ምድር ከመጣች እና የበለጠገ ምርቱን ለመደሰት መብቷን ከተጠቀመች በኋላ፣ አሁንም ቢሆን እረፍት ማግኘት ትችል ዘንድ ቤት ያስፈልጋት ነበር፤ እንደዚህ አይነቱ እረፍት መምጣት የሚችለው በጋብቻ ብቻ ነው፡-

1. የዳንን እና ጌታን የምንወድ ብንሆንም እንኳን፣ ለእረፍታችን የሆነ ቤት እንዲኖረን ጌታ ኢየሱስን እንደ ባላችን በመውሰድ እርሱን ማግባት እና ቤታችን በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከእርሱ ጋር በአንድ ላይ መኖር አለብን—ሮሜ 7፡4፤ 2 ቆሮ. 11፡2፤ ኤፌ. 5፡25-27።
2. ባላችን የሆነው ክርስቶስ እና ቤታችን የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ተገቢ እና በቂ እረፍት የምናገኝበት ሙሉ አሃድ ናቸው (ቁ. 32)።

ሐ. በማቴዎስ 1፡5-6 እና 16 ባለው ብርሃን ሲታይ፣ ሩት እረፍቷን መፈለጓ ክርስቶስን ለማምጣት ለሆነው የዘር ሐረግ መቀጠል ነበር።

መ. ቦዔዝ ለሩት "የቅርብ ዘመድ መሆኔ እውነት ነው፤ ነገር ግን ከእኔ የቀረበ ዘመድ አለ" ብሎ ነገራት—ሩት 3፡12፦

1. በዚህ ጥቅስ ውስጥ የሩት ባል የመጀመሪያው የቅርብ ዘመድ፣ ለሩት የቀረበው ዘመድ፣ ከአሮጌው ሰዋችን ባለዕዳነት (ኃጢአት) ሊዋጀን የማይችለውን እና የማይዋጀንን ተፈጥሮአዊው ሰዋችንን በምሳሌ ያሳያል (4፡1-6)።
2. የሩት ባል ሁለተኛው የቅርብ ዘመድ የሆነው ቦዔዝ የቅርብ ዘመዳችን ለመሆን ደምና ሥጋ የተካፈለውን (ዕብ. 2፡14) እና ከኃጢአታችን ሊዋጀን፣ በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ የተፈጥሮአዊ ሰዋችንን የጠፉ መብት ሊመልስል፣ ከእኛ ጋር ባለው መለኮታዊ ሕይወታዊ ጥምረት አዲሱ ባላችን ሊሆን እና ለመጨመሩ እኛን እንደ አምሳያው ሊወስድ (ሩት. 4፡7-13) የሚችለውን ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል።

## V. መጽሐፈ ሩት ምዕራፍ 4 ሩት ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ሽልማት ስለመቀበሏ ይናገራል፦

ሀ. ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ እንደሆነው የሽልማቷ ክፍል፣ ሩት አማኞችን የሚቤዥ ባል የሆነውን ክርስቶስ በምሳሌ የሚያሳየውን የሚቤዥ ባል አገኘች፤ አሁን በክርስቶስ ውስጥ እንደሆኑ አማኞች፣ ከችግሮቻችን ሁሉ እየታደገን፣ እያዳነን እና ነጻ እያወጣን ያለ ዘላለማዊ፣ የአሁን እና የየዕለት ቤዛ የሆነ ባል አለን።

ለ. ሩት የሚቤዥ ባል ከማግኘቷ በተጨማሪ፣ ከሞተው ባሏ ባለዕዳነት ተዋጅታለች (ቁ. 1፡1-9)፤ ይህ አማኞች ከአሮጌው ሰዋቸው ኃጢአት እየተዋጁ እንዳሉ በምሳሌ ያሳያል፦

1. በሮሜ 6፡6 እና 7፡2-4 መሠረት የሞተው ባል፣ የቀደመው ባላችን፣ አሮጌው ሰዋችን ነው፤ እግዚአብሔር ሚስቱ እንድንሆን ፈጠረን፣ እኛ ግን አመጽንበት፤ እርሱን ተውነው እና የራሳችን ባል የመሆንን ስፍራን ወሰድን።
2. ኃጢአተኛው ባላችን ብዙ ዕዳዎች ጫነብን፣ ክርስቶስን ባገባንበት ቀን ግን፣ ኃያል፣ ሁሉን ቻይ ቤዛ የሆነ ባል ተቀበልን፤ ክርስቶስ ለሁላችንም እንዲህ ያለ ባል እንዲሆንልን ያስፈልገናል፣ እንደልማድ ወደ እርሱ መምጣት እና "ጌታ ኢየሱስ፣ ታስፈልገኛለህ" ማለት አለብን።

ሐ. ሌላኛው የሩት ሽልማት ገጽታ ለክርስቶስ መፍራት የዳዊትን ንጉሣዊ ቤት ለማምጣት በዘር ሐረጉ ውስጥ ወሳኝ ቅድመ ወላጅ መሆኗ ነው (ሩት 4፡13-22፤ ማቴ. 1፡5-6)፤ ይህ የሚያመለክተው ክርስቶስን ወደ ሰው ዘር ውስጥ ለማምጣት ስፍራ እና ብቃት ያለው ሁሉን-ያካተተ እና ሁሉን-ደረስ የሆነ ትርፍ እንደነበራት ነው፤ ከዚህም የተነሣ፣ ወደ ምድር እያንዳንዱ ማዕዘን ክርስቶስን እያመጣ ባለው ሰንሰለት ውስጥ ታላቅ አገናኝ ናት።

መ. ሩት ለክርስቶስ መፍራት በዘር ሐረጉ ውስጥ ወሳኝ ቅድመ ወላጅ መሆን ብቻ ሳይሆን ለክርስቶስ ተሠግዎ በእግዚአብሔር የተፈጠረውን የስብዕና መስመር ጭምር ቀጥላለች፤ የክርስቶስ ተሠግዎ ከዘላለም ውስጥ ወጥቶ ወደ ጊዜ ውስጥ እና በመለኮትነቱ ወደ ስብዕና ውስጥ የመምጣቱ ጉዳይ ነበር፦

1. የክርስትና ሕይወታችን እያንዳንዱ ቀን ክርስቶስን እንደ መንፈስ ወደ ሌሎች ውስጥ በማገልገላችን በኩል ክርስቶስ ወደ ሌሎች ውስጥ ለመወለድ የሚመጣበት የክርስቶስ ተሠግዎ መቀጠል መሆን አለበት—2 ቆሮ. 3፡6።
2. ይህ እንዲሆን፣ ሁላችንም ለክርስቶስ መናገር፣ ክርስቶስን መናገር እና ክርስቶስን ወደ ሌሎች ውስጥ መናገር አለብን፤ ክርስቶስን በዚህ መንገድ ማገልገል ወደ እርሱ መልክ ለመለወጣችን በእርግጠኝነት እኛን እና የምንንከባከባቸውን ሰዎች በገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ መንገድ ይለውጠናል።

© 2021 Living Stream Ministry